ዋለለኝ ሃምሳ ዓመት

ዶ/ር መላኩ ተገኝ

“የብሄሮች ጥያቄ በኢትዮጵያ” ተብሎ በዋለልኝ መኮንን የተጻፈውን ጽሁፍ ሃምሳኛ ዓመት አስታክኮ በሼራተን አዲስ ህዳር 18 ቀን 2012 ዓ.ም በስትራቴጂያዊ ጥናት ተቋም (Institute for Strategic Studies) የተዘጋጀው ሴሚናር በእጅጉ ድንቅ ነበር ማለት እችላለሁ። አቅራቢዎቹ ከተለያየ አቅጣጫ ያቀረቧቸው ፅሁፎች በሳል ከሆነ አመለካከት የመነጩ በመሆናቸው እንዲህ ያለ ጥልቀት ያለው ውይይት ለናፈቀን ፈር ቀዳጅ ነበሩ ማለት ይቻላል። እንዲህ ያሉ በሳል ተናጋሪዎች ያሉባቸው መድረኮች በየጊዜው ቢዘጋጁና የሚዲያ ሽፋን በአግባቡ ቢሰጣቸው አሁን ባገሪቱ ያለውን ውይይት የስነ ስርአት ብቻ ሳይሆን በይዘትም ጥልቅ ትምህርት በመስጠት ሊያሳድጉት ይችላሉ።

ሴሚናሩን በተመለከተ በ ”ኢትዮ ኦን ላይን” ድረ-ገጽ ላይ የተዘገበው ሪፖርት ግን እጅጉኑ አሳዛኝ ነው። ሪፖርት እንዴት እንደማይዘገብ ጥሩ ምሳሌ ነው። አንድ ጋዜጠኛ ከራሱ ስሜት ብቻ ተነስቶ አንድን ሰው ሊያጥላላ የሞከረበት እንጂ በሴሚናሩ ላይ ላልንበሩት ጥሩ ዘገባ ያቀረበበት አልነበረም። ይኼ ደግሞ የጋዜጠኝነት ስህተት “ሀ ሁ” ነው። ጋዜጠኞች በምንም ምክንያት የፖለቲካ ድርጅት አራማጅ መሆን የለባቸውም። አስተያየታቸውን ከዘገባ ለይተው ማቅረብ አለባቸው እንጂ ያልሆነውን ሆነ ብሎ መዘገብ የጋዜጠኝነት ወንጀል ነው። እንዲህ እንዲህ እኮ እየተባለ ነው የሩዋንዳውን ዓይነት ሬዲዮ ሚሌ (አንድ ሚሊዮን ቱትሲዎችን እንዲጨፈጨፉ በቅስቀሳ ከፍተኛ ድርሻ የነበረው ሬዲዮ ጣቢያ) ወደ መሆን የሚኬደው።

ይሄን ካልኩ በኋላ በሴሚናሩ በቅጡ ያልተነሱ ጉዳዮችን ከራሴም ተመክሮ ተነስቼ የሚከተለውን አስተያየት እሰጣለሁ።

## 1. ***መጀመሪያ የብሔር ጥያቄ ለምንና እንዴት ተነሳ?***

በኢትዮጵያ የብሄር ጥያቄን ለመጀመሪያ ጊዜ የተማሪው እንቅስቃሴ ወይም ዋለልኝ መኮንን አይደለም ያነሳው። የብሄር ጥያቄ በኢትዮጵያ ራሱን የቻለ ታሪካዊ ሂደት ነበረው። ጣልያን ከወጣ ጀምሮ ያሉትን የብሄር ይዘት ያላቸውን እንቅስቃሴዎችን ብንቆጥር በኤርትራ፣ ትግራይ፣ ኦጋዴን፣ ሲዳማ፣ ጌዴኦና ባሌ በተለያዩ ጊዜያት በብሄር ማንነት ላይ የተነሱ ህዝባዊ አመጾች ነበሩ። በዚህም ምክንያት መንግስት እነዚህን እንቅስቃሴዎች አንድ በአንድ እየነጠለ ቢመታቸውና በወታደራዊ ፍጥጫው ለጊዜው አብላጫዎቹን ያዳከማቸው እንጂ የኤርትራውና የኦጋዴኑ ግን ለረዥም ጊዜ ቀጥለዋል። የዚህ ሁሉ አመጽ መነሾው የብሄር ጭቆና የሚባለው በብሄር ማንነት ላይ የተመሰረተ አጠቃላይ ኤኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ መድልዖ በተለያዩ ብሄሮች ላይ ይካሄድ ስለነበር ነው። በተለይም በደቡብ፣ ምስራቅና ምእራብ ኢትዮጵያ የሚገኙት የተለያዩ ብሄሮች መሬታቸው ተነጥቆ ለነፍጠኛው የተሰጠበት፣ ተወላጆቹም በገዛ መሬታቸው ገባር እንዲሆኑ ስለተገደዱ፣ በመንግስት ስራ ለመቀጠርም ሆነ ልጆቻቸው ትምህርት ቤት ሄደው እንዲማሩ አማርኛ መናገር ስለነበረባቸው፣ አንዳንዴም በገዢው መደብ ወይም መንግስት ተቀባይነት ለማግኘት ስማቸውን ወደ አማርኛ የሚቀይሩ ነበሩ፣ … ወዘተ። ከላይ ከጠቀስናቸው በብሄር ማንነት ላይ የተመሰረቱ እንቅስቃሴዎች በርካታዎቹ በኤኮኖሚ ጥያቄዎች ላይ (ለምሳሌ መሬታችን ይመለስ፣ ግብር ይቀነስለን፣ ወዘተ… የመሳሰሉት) የተመሰረቱ ነበሩ።

እዚህ ላይ አንድ በግልጽ መቀመጥ ያለበት ጉዳይ አለ። ይኸውም የብሄር ጭቆና ነበር ስንል የገዢው መደብና የመሳፍንቱ መንግስት የአማርኛ ቋንቋን በተቀረው ህዝብ ላይ በመጫናቸው፣ የነዚህ ህዝቦች ቋንቋና ባህል ከቁም ነገር ሳይቆጠር በመቅረቱ፣ ገዢው ክፍል የኢትዮጵያ ቋንቋ ሲል አማርኛ ብቻ በመሆኑ፣ ያገሪቱ ባህል ሲል የአማራና የትግራዩን ባህል በመሆኑ፤ የብሄር ጭቆናውን ባብላጫው አማራና ትግሬ የሆነው የገዢው ክፍል ያካሄደው ነበር። እዚህ ላይ ግልጽ ሆኖ መቀመጥ ያለበት ጉዳይ የብሄር ጭቆናውን የአማራውን ህዝብ ስም ተጠቅሞ ገዢው መደብ ያደረገው የግፍ አገዛዝ እንጂ ጭቆናውን የአማራ ህዝብ ያደረገው ነበር ማለት አይደለም። ዋለልኝም በጽሁፉ ይሄንን ጠቅሶታል። የገዢው መደብ አስከፊውን የብሄር ጭቆና ሲያካሄድ ያማራው ወይም የትግራዩ አርሶ አደርና ድሃው ህዝብ የብሄር ጭቆናው በሚካሄድባቸው ብሄሮች በነበረው

ድህነት (አንዳንዴም በባሰ) እኩል ይማቅቅ ነበር። ለነገሩ ወላይታ ወይም ሲዳማ፤ አፋር ወይም ሶማሌ ምን እንደሆነ የጠገዴው፣ የወልቃይቱ ወይም የአድዋው አርሶ አደር እስከ መፈጠሩም አያውቀው እንኳን የብሄር ጭቆና ሊያካሄድበት።

ከላይ የጠቀስናቸው የጭቁን ብሄር አመጾች በየጊዜው የተነሱ እንደመሆናቸው የኤርትራው አመጽ እያየለ በመምጣቱ መንግስት በብዙ ሺ የሚቆጠር ሰራዊት በማፍሰሱና ጦርነቱም በመጋጋሉ ጉዳዩ በግልጽ ያገሪቱ የፖለቲካ ችግር ነበር። በዚህ ላይ አንዴ ቦግ አንድ እልም የሚለው በኦጋዴን የነበረው እንቅስቃሴ የኢትዮጵያን መንግስት ከሶማሊያው መንግስት ጋር ቢያንስ ሶስት ጊዜ እንዲዋጋ አድርጎታል። ይሄም ራሱን የቻለ የፖለቲካ ችግር ነበር። በዚህ ላይ አንዴ ቦግ አንዴ ጥፍት የሚሉ አመጾች በጌዴዎና ሲዳማ ሲካሄዱ በጎጃምም የአርሶ አደሩ አመጽ ነበር። የተማሪው እንቅስቃሴ ደግሞ ባገሪቱ ባሉት ችግሮች ላይ ተመርኩዞ ጥያቄዎቹን ለመንግስት ያቀርብ ነበር፣ ሰላማዊ ሰልፍም እያደረገ ተጋፍጧል። የተማሪው እንቅስቃሴ ራሱ የተዳዘባቸው ጎዳናዎች እንዳሉ መታየት አለበት። “መሬት ለአራሹ ሊሰጠው ይገባል” ካለበት ጊዜ ጀምሮ መንግስትን በስር ነቀል አመለካከት ይቃወመው ጀመር። ለዚህ ነው የተማሪው እንቅስቃሴ የብሄር ጥያቄን በተለያዩ ጊዜያት አንስቶ የተለያዩ አቋሞችን ወስዶ የነበረው። ከላይ እንዳሳየነው የብሄር ጥያቄ በተማሪው እንስቅሴ የተነሳው አንድ ቀን ዋለለኝ ተነስቶ የተባለውን ወረቀት ስለጻፈ አይደለም። ከዋለልኝ በፊት ጥያቄው በተለይም በኤርትራና በባሌ በተቀሰቀሰው አመጽ የተነሳ ባንድ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጉባኤ ላይ ተነስቶ ውሳኔ ተላልፎበታል። በ1959 ዓ.ም የተሰበሰበው 6ኛው የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብሄራዊ ማህበር (National Union of Ethiopian University Students) ጉባኤ ተደርጎ በኤርትራና በባሌ የተነሱት አመጾች ጸረ-ኢምፔሪያሊስትና ጸረ-ፊውዳል ስላልነበሩ መደገፍ የለባቸውም ብሎ ነበር። ከዚያም ጋር በተያያዘ አንዳንድ ተማሪዎች ስለብሄር ጥያቄ የተለያዩ ጽሁፎችን ጽፈዋል (ለምሳሌ ገብሩ ገብረወልድ Tribalism: the Feudal Tactic of Divide and Rule)። ይሄ ሁሉ ዋለለኝ ከመጻፉ በፊት ነው። ይሄን ታሪካዊ ቅደም ተከተል ማረጋገጥ ወሳኝ ነው።

በ1961 ዓ.ም ላይ የተማሪው ሰልፍ ሲደረግ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰልፎች ካዲሳባ ወጥተው በየጠቅላይ ግዛቱ ያሉትን ተማሪዎች አስነሳ። እንቅስቃሴው ያዲሳባ ብቻ ሳይሆን ብሄራዊ ሆነ። መንግስትን ፍርሃት ውስጥ የከተተው ይኼው የተማሪ እንቅስቃሴ መስፋፋት ነበር። በዚህ ምክንያት ነበር በተማሪ እንቅስቃሴ ጉዳይ በይፋ ምንም ተናግረው የማያውቁት ንጉስ ሁለት ጊዜ ንግግር ያደረጉት። በመጀመሪያው ንግግራቸው “ባልበሰለ አእምሮ ያገሪቱን ችግር ለመተንተን መሞከር” ተገቢ እንዳልሆነ ሲገልጹ ዋለለኝ በድፍረት “ያገሪቱን ችግር የሚፈታው የጃጀ አእምሮ እንዳልሆነ” ገለጸ። የዋለለኝ ጽሁፍ በጊዜው እንቅስቃሴው ውስጥ ለነበርነው አንድ ምእራፍ አሲዞናል፤ ከዚያን ጊዜ ወዲህ የተማሪው እንቅስቃሴ የምር የሆነ እንቅስቃሴ ሆኖ መምጣቱንና ተማሪውም ደፍሮ እንዲታገል አድርጎታል። ለመጀመሪያ ጊዜ ተማሪዎች በፖለቲካ “ወንጀል” ተከሰው ብዞዎቹ የስድስት ወር እስራት፣ አምስቱ -ዋለልኝን ጨምሮ- አምስት ዓመት፣ ሶስቱ ደግሞ የ ሰባት ዓመት ተኩል እስራት ተፈረደባቸው። ተማሪው ጓዶቻችን ካልተፈቱ አንማርም ስላለ፣ መስከረም ላይ ተማሪዎች በሙሉ ተፈቱ።

ትምህርት ካቋረጡት ተማሪዎች በርካቶቹ ስለሶሻሊዝም ንባብ ያደረጉትና ማርክሲዝም በሰፊው ተቀባይነት ያገኘበት ወቅት ሆነ። እነዚህ ሁኔታዎች መንግስትን ስላሰጉት ተማሪውን በብሄር ለመከፋፈል ተነሳ። በዊንጌትና ሀረር በሚገኘው የመምህራን ማሰልጠኛ ት/ቤት ውስጥ ትግርኛ ተናጋሪና ትግሪኛ ተናጋሪ ባልሆኑ ተማሪዎች ግጭት እንዲቀሰቀስ ተደረገ። ሁለተኛው የመንግስት ስትራቴጂ ተማሪዎችን ተንኩሶ ሰልፍ ሲወጡ የሚፈልጋቸውን መርጦ ሰልፍ ላይ መግደል ነበር። እነዚህን ሁለት ስትራቴጂዎች የዓላማያ ኮሌጅ ተማሪዎች ማህበር ፕሬዚዳንትና እኔ (ያኔ እኔ የማህበሩ ም/ፕሬዚዳንት ነበርኩ) ልኡክ ሆነን አዲሳባ መጥተን ከነጥላሁን ግዛው ጋር በጉዳዩ ላይ ተወያይተናል። በዚያ ግንኙነት ወቅት መጀመሪያ ስለ ብሄር ጥያቄና እንዴት በነሱ በኩል እንደታየ ገለጻ አደረጉልን። ሁለተኛው ጉዳይ ማለትም መንግስት የሚፈልጋቸውን ተማሪዎችን ሰላማዊ ሰልፍ ላይ ለመግደል ስለነበረው እቅድ በሰፊው አስረዱን። ጥላሁን “እኛ ሰላማዊ ሰልፍ የምናደርገው በራሳችን እቅድ እንጂ መንግስት ስለጎነተለን መሆን እንደሌለበት” አስረዳን።

እንደተረዳነው የተማሪው መሪዎችን መንግስት ተማሪውን የመከፋፈል እቅዱ አስጊ ሆኖባቸው ነበር። ምክንያቱም ተማሪውን ለመከፋፈል ቀላሉ መንገድ በብሄር መከፋፈል ስለሆነ ነበር። እኔ እንደተረዳሁት ያኔ የብሄር ጥያቄ ያበጠው ይፈንዳ በሚል እሳቤ እንዲነሳ ካደረጉት ምክንያቶች አንደኛው ይኸው የተማሪው የመከፋፈል አደጋ እየመጣ ስለነበር ይመስለኛል። ዋናው ምክንያት ግን ባገሪቱ የተነሱት ብሄር ተኮር እንቅስቃሴዎች እየጋሙ ስለነበርና መንግስትም በነሱ ላይ "ከሃዲዎች፣ አገራቸውን ለአረብ ዶላር የሸጡ" ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉ ፕሮፓጋንዳዎች ያደርግ ስለነበር ስለነዚህ እንቅስቃሴዎች ተማሪው ትክክለኛው ግንዛቤ እንዲኖረው ለማድረግም ነበር። በዚያውም በተማሪው መሃል የነበረው የማን አህሎኝነት (chauvinism) ዝንባሌ ከመንግስት ቅስቀሳ ጋር ተደማምሮ የተማሪውን እንቅስቃሴ ይበልጥ ሊከፋፍለው ይችላል የሚል ስጋትም ነበር። የብሄር ጥያቄ የተነሳበት ዋነኛዎቹ ምክንያቶች ከላይ የዘረዘርናቸው ጉዳዮች ነበሩ።

## 2. የብሄር ጥያቄ በኢትዮጵያ (The Question of Nationalities in Ethiopia)

"የብሄር ጥያቄ በኢትዮጵያ" የተሰኘውን ጽሁፍ ማን ጻፈው? ከፖለቲካዊ አስተያየት አንጻር ፅሁፉን ማን ጻፈው የሚለው አስተያየት ጨርሶ ቦታ የለውም፡፡ ምክንያቱም ዋናው ጉዳይ የችግሮቹ ቁም ነገሮች መቅረባቸው ነውና። አሁን አንዳንድ ሰዎች "የብሄሮች ጥያቄ በኢትዮጵያ" የሚለውን ጽሁፍ ዋለልኝ እንዳልፃፈው ሲናገሩ ይደመጣሉ። በሲ.አይ.ኤ. ተጽፎ እንደተሰጠው ይናገራሉ፡፡ እነዚሁ ሰዎች ለምን ፅሁፉን ዋለልኝ እንዳልጻፈው ሲጠየቁ "የእንግሊዝኛው ደረጃ ከፍተኛ ስለሆነ አንድ ኢትዮጵያዊ አይጽፈውም" ይላሉ። ይኸው የፈጠራ ወሬ በሀሙሱ (ህዳር 18 ቀን2012 ዓ.ም) ስብሰባ ላይ ተነስቶ ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀና ዶክተር ዲማ ነገዎ መልስ ሰጥተውበታል። የዘንድሮ ውሸት ፈጣሪዎች ሁሉንም በራሳቸው የእውቀት ደረጃ ስለሚገምቱ ውሸቱንም በዚያው ፈብርከውታል። በዚያን ጊዜ በት/ ቤቶችና ኮሌጆች የነበረው የእንግሊዝኛ እውቀት ደረጃ ከፍተኛ ነበር። በኛ ጊዜ ከአማርኛ በስተቀር ሁሉንም ትምህርቶች በእንግሊዝኛ መማር የጀመርነው ገና ሶስተኛ ክፍል ስንገባ ነው። መጀመሪያ በህንድ አስተማሪዎች፣ ከዚያ በኋላ ሁለተኛ ደረጃ ስንገባ ደግሞ እንግሊዝኛ እንደ ቋንቋ ባብላጫው በአሜሪካውያንና እንግሊዞች ነው የተማርነው። ስለሆነም ገና ሁለተኛ ደረጃ እንደገባን እንግሊዝኛ አቀላጥፈን እንናገር ነበር።

ዩኒቨርሲቲ ደግሞ የተማሪዎች ማህበራት ስብሰባ ሳይቀር የሚካሄደው በእንግሊዝኛ ነበር። ያዲሳባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበርም ሆነ እኔ የነበርኩበት ዓለማያ ኮሌጅ የተማሪዎች ማህበር ስብሰባ የሚካሄዱት በእንግሊዝኛ ነበር። ክርክሩ፣ ጭቅጭቁ፣ ውይይቱ በእንግሊዝኛ ነበር። ከዚያም በላይ በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ሚና የነበራቸው ደግሞ ባንድ በኩል፣ ማርክሲዝምን ለማወቅ እንዲሁም በዓለም ላይ ያለውን የፖለቲካ ሁኔታ ለመከታተል እጅግ ብዙ ማንበብ ስለነበረባቸውና ማሳወቅም ስለነበረባቸው የሚነበበውም ጽሁፍ አብዛኛው በእንግሊዝኛ ስለነበር የተማሪው እንቅስቃሴ መሪዎች የእንግሊዝኛ ችሎታ ከሌሎቹ የላቀ ነበር። ለምሳሌ ባንድ ወቅት አውሮፓ እያለን የየካቲቱ አብዮት እንደፈነዳ በዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን መጽሄት አዘጋጅነቴ ስለሁኔታው መግለጫ ሳወጣ መግለጫው ከመውጣቱ በፊት እንዲያው ስለቋንቋው ዕርግጠኛ ለመሆን አንዲት አሜሪካዊት ጓደኛዬን እስቲ ቋንቋውን እዩልኝ አልኩና ጹሁፉን ሰጥተኋት። አነበበችና "እኔ ይሄን ምንም ላርም አልችልም፣ እንዲያውም የተማርኩበት ነው" ያለችኝ ትዝ ይለኛል። እኔ ያኔ የትምህርት ደረጃዬ ዓለማያ የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ነበርኩ። ባጭሩ ያኔ የእንግሊዝኛም ሆነ የጠቅላላው የትምህርትና የጠቅላላ እውቀት ደረጃው ከፍተኛ የበር፡፡ ዋለለኝ መኮንን ባማርኛም በእንግሊዝኛም የጽሁፍ ችሎታው ከፍተኛ ነበር። ይሔ ብቻ ሳይሆን በዚያን ጊዜ ባገር ወስጥና በውጭ አገር በእንግሊዝኛ ይጻፉ የነበሩ የተማሪ ማህበር ፅሁፎችን መመልከቱ ይበቃል።

## 3. ***ጽሁፉን ዋለልኝ መኮንን ብቻውን ነው የጻፈው?***

ራሱ ዋለልኝ በዚያው ጽሁፉ እንደሚገልፀው በወቅቱ በብሄር ጥያቄ ላይ በድብቅ ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ ይህም ማለት ያ ጽሁፍ ከዋለልኝ አእምሮ ብቻ ፈልቆ የወጣ እንዳልሆነ ግልጽ ያደርገዋል። ተደጋግሞ እንደተገለጸው ጽሁፉን ዋለልኝና በጣም ጥቂቶች (ለምሳሌ ዮሃንስ ስብሃቱ) ረቂቁን እንደጻፉትና ከዚያ በኋላ

ሌሎችም ሃሳባቸውን የሰጡበት ለመሆኑ እኔ ራሴ አውቃለሁ። ስለዚህ የብሄር ጥያቄ በኢትዮጵያ በተሰኘው ጽሁፍ ውስጥ የተካተቱትን ሃሳቦች በሙሉ ዋለልኝ ብቻውን እንዳላፈለቀው ሊታወቅ ይገባል።

**4. ዋለልኝ ያማራን ህዝብ እንዳጥላላና የአማራን ህዝብ ጨቋኝ አርጎ እንዳቀረበ አርገው የሚጽፉም አልጠፉም።**

ይሄም የዋለልኝን ጽሁፍ አለመረዳት ነው። የገዢው መደብ የአማራውን ህዝብ ስም እየተጠቀመ የብሄር ጭቆናን እንዳካሄደ ዋለልኝ ይገልጻል። ከተናጋሪዎቹም መሃል ለምሳሌ ፕሮፌሰር ማርታ ኩምሳ ዋለልኝ አማራ ሆኖ የአማራውን የብሄር ጭቆና ተቃውሞ መጻፉ ያስመስግነዋል ይላሉ። ዋለልኝ የውሸት ብሄርተኝነት (fake nationalism) የሚለውን ከአማራ የበላይነት ስሜት ጋር አያይዞ ይወቅሳል። ዋለልኝ የሚወቅሰው እኮ የአማራን ህዝብ አይደለም፣ በአማራው ስም ገዢው መደብ ያቀነቅን የነበረውን የውሸት ብሄርተኝነትን ነው።

**5. ዋለልኝና ወያኔ፡- “ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ”**

አንድ ድርጅት ያንድን ሰው ሃሳብ ነው የምከተለው ሲል ማየትና መመርመር ያለብን ያ ድርጅት የሚለፍፈውን ብቻ ሳይሆን ሃሳቡን ተቀብያለሁ የተባለለትን ሰው ጽሁፍንም በሚገባ መርምሮ በዕርግጥ ድርጅቱ ከሚለውና ከሚሰራው ጋር ማስተያየት ይኖርብናል። እንዲያው አንድ ድርጅት የዚህ ወይም የዚያ ሰው ተከታይ ነኝ ስላለ በርግጥ ሃሳቡም ስራውም ያ ሰው እንዳለው ነው ማለት አይደለም። ለምሳሌ መላ ዓለምን ያናወጠው የቦልሼቪክ አብዮት መሪ የነበረው ሌኒን ከፖለቲካ ፍልስፍና አቅጣጫ ቢታይ የካርል ማርክስን ሃሳብ ስራ ላይ አውሏል ማለት አይቻልም። ስታሊንም እንኳን የማርክስን የሌኒንንም ሃሳብ አልተከተለም። ግን ሌኒንም በማርክስ ይምል ይገዘት ነበር፤ ስታሊንም በሌኒን ይምል ይገዘት ነበር። በኔ አስተያየት ግን መሰረታዊ በሆነ የፖለቲካ ዶክትሪን ማርክስ ወዲህ ሌኒን ወዲያ ነበሩ። ስታሊን ደግሞ ከሌኒንም ብሶ መሰረታዊ በሆኑ በማርክስ የፖለቲካ ዶክትሪን ጥሰት ብቻ ሳይሆን ሶሻሊዝም እንዲጠላ ያደረገ ወንጀለኛ ነው። ከስታሊን በኋላ ደግሞ ማኦ፣ ከማኦ በኋላ ኪሚል ሱንግ (የኮሪያው) እንዲሁም የአልቤኒያው እንቨር ሆጃ መጡና ሶሻሊዝም እንዲጠላ ብቻ ሳይሆን ራሱን የሶሻሊዝምን አመለካከት ጭምልቅልቁን አውጥተው ሰዎች እንደ ጣኦት እየተመለኩ ሶሻሊዝም እንዲጠላ ብቻ ሳይሆን እንዲፈራም አደረጉ። የኛው ጉድ መንግስቱ ሃይለማሪያም ደግሞ በሶሻሊዝም ስም ብዙ ህዝብ ከመጨረሱ የተነሳ ሶሻሊዝም የወንጀለኞች አመለካከትም እንዲመስል አደረገ። ስለዚህ ሰዎች የዚህ ወይም የዚያ ፈላስፋ ተከታይ ነን ስላሉ በርግጥም በሚሉትና በተለይም በሚሰሩት ይገመታሉ እንጂ ያንን ፈላስፋ ይከተላሉ ማለት አይደለም።

ዋለልኝና ወያኔም እንዲሁ። ከመንግስት አወቃቀር አንጻር ዋለልኝ አንድ ኢጋሊቴሪያን የሆነ ሁሉንም በኩል ደረጃ የሚያሳትፍ መንግስት ያስፈልገናል ሲል ወያኔ ግን ገና ሲጀምር የኢትዮጵያ ብሄሮች መጀመሪያ ተበታትነው በኋላ ከፈለጉ አንድ ላይ ይሆናሉ ነው ያለው (የ1976 ማኒፌስቶ)። ወያኔ ስልጣን ሲይዝ ደግሞ ዋለልኝን የተከተለ መስሎ ማወናበድ ቢሞክርም ዋናው ስትራቴጂ ግን፤ እኛ የንኡሳን መንግስት (ሁሌም በጠባብ አመለካከት ስለብሄር ብቻ ስለሆነ የሚያስቡት) ስለሆንን በኢትዮጵያ ደረጃ ስልጣን ላይ ለመቆየት በተለይ ትላልቅ የሆኑ ብሄሮችን እየከፋፈልንና እያናከስን ግን የዚህ ግጭት ዳኛ መስለን የምንታይበት የፖለቲካ ስልጣን መዋቅር ማዋቀር አለብን ከሚል ቀመር ተነስተው ነው የብሄር ፌዴራሊዝምና የብሄር ክልል አስተዳደር የጀመሩት።

በ1996 ዓ.ም ላይ ከአንድ የወያኔ አመራር ከነበረ ሰው ጋር ላንድ ጥናት ቃለ መጠይቅ ሳደርግ የዋለልኝን ጽሁፍ እንዳላነበበው ሲነግረኝ በእጅጉኑ አስገረመኝ። ሰውዬው ያነበበው የብርሃነ መስቀልን ጽሁፍ (በጥላሁን ታከለ ስም የወጣው) ብቻ ነበር። ወያኔዎች እንኳን የዋለልኝን መልእክት ሊከተሉ ቀርቶ በቅጡም ያነበቡት አይመስለኝም፣ ቢያነቡትም የገባቸው አይመስለኝም። ስለዚህ ወያኔዎች በተለይ መጀመሪያ ገደማ ጠዋት ማታ ዋለልኝ ዋለልኝ ስላሉ የዋለልኝ ሃሳብ ተከታዮች ነበሩ ማለት አይደለም። ዋለልኝ ከሁሉ አስቀድሞ ሴንትራሊስት ነበር። ስለዚህም በብሄርና በቋንቋ እየተለያዩ በክልል መካለል የሚለውን ሃሳብ በፍጹም የሚደግፈው አይደለም። በርግጥ በሱ ጊዜ የፖለቲካ ስልጣን የመጨበጥ ጥያቄ

ወዲያው የሚነሳበት ሁኔታ ስላልነበረ ምን ዓይነት መንግስት እንደሚያስፈልግ ግን ዋለለኝ ጠቁሟል፤ **ሁሉንም በእኩልነት የሚያሳትፍ ኢጋሊቴሪያን መንግስት።**ከዚህ በላይ ሴንትራሊዝም የለም።

**5. ማርክሲዝምና የብሄር ጥያቄ እንዴት ነበሩ?**

ባገራችን ማርክሲዝም በብሄር ጥያቄ ላይ ያለው አስተያየት ተብሎ የሚቀርበው ሌኒንና ስታሊን ያሉት ብቻ ነው። ይኼ ፈጽሞ የተሳሳተ ማርክሲስቶች በብሄር ጥያቄ ላይ ስለነበራቸው አስተያየት የተዛባ አመለካከት የሚሰጥ ነው። እንዴት?

ከሁሉ አስቀድሞ የብሄር ጥያቄ በአውሮፓ ሁኔታ ሲነሳ ካፒታሊዝም ወደ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም (ኢምፔሪያሊዝም የሚባለው) ደረጃ የገባበት ወቅት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ባውሮፓ ውስጥ በተለያዩ አገሮች ጥያቄው ስለተነሳ ነበር ሶሻሊስቶች በጉዳዩ ጉባኤ አርገው በ1896 ዓ.ም አንድ ውሳኔ አሳለፉ። ውሳኔው የብሄር እንቅስቃሴዎችን ተገቢነት የሚደግፍ ነበር። ከዚህ በጣም አጠቃላይ ከሆነ ውሳኔ ሌላ ማርክሲስቶች በዝርዝር ገብተው በብሄር ጥያቄ ላይ የተወሰነ አስተያየት አልነበራቸውም። ለዚህ ነው በተለያዩ አገሮች የነበሩ ማርክሲስቶች በብሄር ጥያቄ ላይ የተለያየ አስተያየት የነበራቸው። በኦስትሪያ እነ ኦቶ ባወር፣ በጀርመን እነ ካርል ኮትስኪ፣ በሩሲያ ቦልሼቪኮችና ሜንሼቪኮች…እነዚህ ሁሉ የተለያየ አተረጎጓጎምና አስተያየት በብሄር ጥያቄ ላይ ነበራቸው።

የተማሪው እንቅስቃሴ የብሄር ጥያቄን ሲያነሳ የማርክሲዝም አስተያየት ነው ብሎ የተንደረደረው የቦልሼቪኮችን አመለካከት ብቻ ይዞ ነው። የሌሎቹን ከነመኖራቸውም አላነሳቸውም። የሆነው ሆኖ የሌኒንና የስታሊንን አመለካከት እንኳን ብንወስድ በጊዜው በዓለም ከነበሩት ማርክሲስቶች ስንቶቹ ከሌኒንና ስታሊን ጋር እንደተስማሙ በውል አይታወቅም። ባብላጫው ግን ሌኒንና ስታሊን በብሄር ጥያቄ ላይ ተቀባይነታቸው እጅግ ውሱን ነበር። በምእራቡ ዓለም ከነበሩት ማርክሲስቶች ከሌኒን ጋር የተስማሙ አልነበሩም።

ቦልሼቪኮች ስልጣን ከያዙ በኋላ ገናናነታቸውን በመጠቀም ሶስተኛውን የዓለም አቀፍ ኮሙኒስት እንቅስቃሴ ጉባኤ በሞስኮው በ1920 ዓ.ም ጠርተው ነበር። ከዚህ ጉባኤ አጀንዳዎች አንደኛው የብሄር ጥያቄ ነበር። በዚህ ጉባኤ ሌኒን ተቃውሞ ገጥሞት ነበር። በተለይም ሮይ የተባለው የህንድ ኮሙኒስቶች ተወካይ የሌኒን ሃሳብ ተቀባይነት እንዳይኖረው አድርጓል። በቦታው ይልቅ ያኔ በቅኝ ግዛቶች የተነሱ አያሌ ፀረ-ኮሎኒያል ትግሎች ስለነበሩ የብሄር ጥያቄ ከዚህ ከፀረ-ኮሎኒያል ትግል አንጻር መታየት አለበት ተብሎ ባዲስ መልክ እንዲታይ ሆነ እንጂ የዓለም ኮሙኒስቶች እንቅስቃሴው ወደ ድሮው የሌኒንና ስታሊን ትንታኔ አልተመለሰም። ከዚያ በኋላ በኮሙኒስት ፓርቲዎች የተመሩትን ፀረ-ኮሎኒያል ትግሎችን ብንመለከት የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ የሌኒንና ስታሊንን አመለካከት አልተከተለም። በሆ ቺ ሚን የሚመራው የቬትናም ትግልም ጉዳዩን የማይኖሪቲስ ጥያቄ እያለ ነው ያለፈው። ስለዚህ የሌኒን የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል የሚለው በዓለም ኮሙኒስቶች ዘንድ ጨርሶ ተቀባይነት አልነበረውም።

በተረፈ በእውቀትም ሆነ በተመክሮ፣ ባመለካከትም ሆነ በትንተና፣ በሀቀኝነትና በህዝብ ወገንተኛነት፣ በድፍረት ጨቋኞችን በመታገልና በማጋለጥ ወደር የማይገኝለትን ዋለልኝ መኮንንን በማያውቁትና እሱ የጻፋቸውን እንኳ ሳያነቡ (ቢያነቡም ሳይረዱ) በየሜዳው ማንም ሃላፊነት የጎደለው ሁሉ የሚነዛውን ወሬ በሚያሳፍር ድንቁርናና ስንፍና አምኖ ይህንኑ ውሸት መልሶ በሚዲያ ማስተጋባት ኢትዮጵያዊ ጨዋነትም ሆነ የጋዜጠኝነት ስነምግባር የጎደለው ነው።

(ለፌስ ቡክ አንባቢዎች እንዲመች አድርጌ ያቀረብኩት፡- ስለሺ ቱጂ)

